ቀን ጥር 03 2015
Date
ቁጥር ፈ166/15
Ref.No

በዝርዝር ለተመለከተቱት በሙሉ

በያሉበት

ጉዳዩ፡- <u>መመሪያ ስለመላክ</u>፤

የራስ ታክስ ስሌት ጥያቄ አቀራረብና አፈጻጸም ተሻሽሎ የወጣን መመሪያ ቁጥር 181/2015 ከዚህ ጋር በማያያዝ የላክን ስለሆነ በመመሪያው መሠረት እንዲፈፀም አስታውቃለሁ።

ከሠላምታ ጋር

አዶናይ ለም ነገ·ሌ አለ.
ሚኒስትር

<u>ግልባጭ፡-</u>

- ለሚኒስትር ጽ/ቤት
- ለታክስ ስርአርት ዘርፍ
- ለታክስ አኘሬሽን ዘርፍ
- ለተቋማዊ አቅምና ድጋፍ ቢሮ

<u>ገቢዎች ሚኒስቴር</u>

Phone: +251 11 662 98 00/ 01/02/03/04/05/06/07/08 **Fax:** /+251 11 662 98 17
face book page: ministry of revenues. **FBP:** mor Ethiopia **Twitter:** erca@twitt
web site: http//www:erca.gov.et **P.o. Box:** 2559 Addis Ababa, Ethiopia

የራስ ታክስ ስሌት ጥያቄ አቀራረብና አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር
181/2015

ጥር 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ሰበረ ኦበበ ሙ
የሚኒስትር ሕግ ,

የራስ ታክስ ስሌት ጥያቄ አቀራረብና አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 181/2015

ማንኛውም ታክስ ከፋይ እራሱ አስልቶ ያቀረበውን የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ የታክስ ባለሥልጣኑ ሲፈቅድለት ሊያሻሽል እንደሚችል በአዋጁ የተደነገገ በመሆኑ እና፤

የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ እንዲሻሻል በታክስ ከፋዩ ማመልከቻ ሲቀርብ ማሻሻያው የሚፈቀድበትን አሰራር በግልጽ ማስቀመጥ በማስፈለጉ፣

ገቢዎች ሚኒስቴር በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 29(3) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የራስ ታክስ ስሌት ጥያቄ አቀራረብና አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 181/2015" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም፡-

1/ "የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ የማሻሻያ ጥያቄ" ማለት ታክስ ከፋዩ በራሱ አዘጋጅቶ ባቀረበው የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ላይ ሊደረጉ ይገባል ብሎ የሚያምንባቸውን ማሻሻያዎች እና ምክንያቶቹን በመግለጽ የሚያቀርበው የማሻሻያ ጥያቄ ነው፡፡

2/ "ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት" ማለት በተወሰነ አካባቢ በተከሰተ ጦርነት፣ ዝርፊያ፣ ጎርፍ፣ ቃጠሎ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ መብረቅ፣ ተምች ወይም ሌላ ተመሣሣይ

አባረ አለበ መን
የማ[illegible]ስትር ሐላ
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Doc

ክስተት ምክንያት ታክስ ከፋዩ ለታክስ ስሌት የሚያስፈልገውን ሰነድ ማግኘት ሳይችል የሚቆይበት ሁኔታ ሲያጋጥም ነው፡፡

3/ "ቦርድ" ማለት በፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ ደረጃዎች ድንጋጌ መሠረት የውጭ ኦዲተሮች የሚያዘጋጁትን የሂሳብ ሪፖርት መርምሮ ማረጋገጫ የሚሰጥ የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝ ኦዲት ቦርድ ነው፡፡

4/ "የታክስ ባለሥልጣን" ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር፣ የአዲስ አበባ ገቢዎች ባለሥልጣን እና የድሬዳዋ ገቢዎች ባለሥልጣን ማለት ሲሆን ቅ/ጽ/ቤቶቻቸውንም ይጨምራል፡፡

5/ "ሚኒስቴር" ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር ሲሆን የሚኒስቴሩን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ይጨምራል፡፡

6/ "ሚኒስትር" ማለት የገቢዎች ሚኒስትር ነው፡፡

7/ "አዋጅ" ማለት የፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ነው፡፡

8/ "ደንብ" ማለት የፌደራል ታክስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 407/2009 ነው፡፡

7/ በዚህ መመሪያ ውስጥ ትርጉም ያልተሰጣቸው ቃላትና ሀረጎች በታክስ አስተዳደር አዋጅ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

9/ በዚህ መመሪያ በወንድ ጾታ የተገለጸው ለሴት ጾታም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

3. <u>የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ እንዲሻሻል ጥያቄ በሚያቀርብ ማንኛውም ታክስ ከፋይ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

Ethiopian Ministry of Revenues
Record & Document Management

ክፍል ሁለት

የራስ ታክስ ስሌት ስለሚሻሻልበት ምክንያትና አቀራረብ

4. የታክስ ስሌት የሚሻሻልበት ምክንያት

1/ ታክስ ከፋዩ ራሱ ያዘጋጀው የታክስ ስሌት ማስታውቂያ እንዲሻሻልለት ሲያመለክት በሚከተሉት ምክንያቶች የታክስ ባለሥልጣኑ ሊያሻሽልለት ይችላል፡፡

ሀ) የሂሳብ ስሌት ስህተት፤

ለ) የገቢ እና የወጪ አመዘጋገብ ስህተት፤

ሐ) ከሒሳብ መደብ አመራረጥ (Chart of Account) ጋር የተያያዘ ስህተት ሲኖር፤

መ) የጆርናል ምዝገባ ስህተት ሲኖር፤

ሠ) ሂሳብ ወደ ሌጀር ሲተላለፍ የተከሰተ ስህተት ሲያጋጥም፤

ረ) ከሒሳብ ማስተካከያ (Adjusting Entry) ጋር የተያያዘ ስህተት ሲያጋጥም፤

ሰ) በሒሳብ መዘገብ ላይ ሳይመዘገብ የተዘለለ የገቢና ወጪ ሰነድ ሲኖር፤

ሸ) የሀብትና ንብረት ቆጠራ ስህተት፤

ቀ) የሒሳብ አያያዝ ዘዴ ስህተት፤

በ) በውጭ ኦዲተሮች እና በቦርዱ በቀረበ የኦዲት ምርመራ ሪፖርት የቀረበ ማስተካከያ፤

ተ) ሦስተኛ ወገን በሚሰጠው ማረጋገጫ ወይም በፍርድ ቤት በሚሰጥ ውሳኔ መሰረት በሂሳብ መዝገቡ ላይ ማስተካከያ ማድረግ ሲያስፈልግ፣

ቸ) በታክስ ሕግ ያልተፈቀደ ወጪ በተቀናሽነት በመያዙ ምክንያት በተፈጠረ ስህተት፤

ኀ) የግልና የንግድ ሒሳቦች በመቀላቀላቸው የተፈጠረ ስህተት ሲያጋጥም፤

ነ) በታክስ ማስታወቂያ ቅፅ ላይ የአመዘጋገብ ወይም የአገላለጽ ስህተት ሲያጋጥም፣

ኘ) በታክስ ወይም በተለይ በኤክሳይዝ ታክስ ሂሳብ አያያዝ ላይ የማምረቻና አስተዳደራዊ ወጪዎች ተፋልሰውና ባልተገባ ቦታ ላይ ተመዝግበው ሲገኙ፤

አ) ከተጨማሪ እሴት ታክስ እና ከኤክሳይዝ ታክስ ጋር በተያያዘ በታክስ ማስታወቂያ ውስጥ ሳይካተት የቀረ ታክስ ወይም ከተቀናሽ ሂሳብ አያያዝ እና የተመላሽ ጥያቄ ጋር በተያያዘ ስህተት ሲያጋጥም፤

Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No 1

ሳቢረ አበበ መንግስቱ
የሚኒስትር ሕግ ፣

ከ) ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ለታክስ ስሌት የሚያስፈልጉ ሰነዶች ሳይሟሉ በመቅረታቸው ታክስ ከፋዩ በእጁ ያሉትን ሰነዶች ብቻ መሠረት በማድረግ ሌላውን ታክስ በግምት ባሰላው የራስ ታክስ ስሌት መሠረት አሳውቆ ከከፈለ በኋላ የተሟላ ሰነድ ማቅረብ በቻለበት ጊዜ፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተዘረዘሩት ምክንያቶች የተለየ እና በሚከፈለው የታክስ መጠን ላይ ለውጥ ሊያስከትል የሚችል አሳማኝ ምክንያት ሲቀርብ ስራ አስኪያጁ የራስ ታክስ ስሌት ማሻሻያ እንዲደረግ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

5. <u>የራስ ታክስ ስሌት እንዲሻሻል የሚቀርብ ማመልከቻ</u>

1/ ታክስ ከፋዩ ያቀረበው የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ እንዲሻሻልለት በሚያቀርበው ማመልከቻ ላይ የታክስ ስሌቱን ለማሻሻል ምክንያት የሆኑትን ጉዳዮች በዝርዝር በመጥቀስ ጥያቄውን በጽሁፍ ለታክስ ባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

2/ ታክስ ከፋዩ ያቀረበው የታክስ ስሌት ማሻሻያ ጥያቄ ማመልከቻው ከቀረበበት ቀን በፊት ባሉ 5 ዓመታት ጊዜ ውስጥ በነበሩ የራስ ታክስ ስሌቶች ላይ ለውጥ የሚያመጣ ከሆነ የሁሉም ዘመናት የታክስ ስሌት ማሻሻያ ጥያቄዎችን በአንድነት ሊያቀርብ ይችላል፡፡

6. <u>የማመልከቻው ይዘት</u>

1/ በራስ ታክስ ስሌት ላይ ማሻሻያ እንዲደረግ የሚቀርበው ማመልከቻ የሚከተለው ይዘት ይኖረዋል፡፡

(ሀ) የታክስ ስሌት ማሻሻያ እንዲደረግ የተጠየቀበትን የታክስ ዓይነት እና የሂሳብ ጊዜ፤

(ለ) ማሻሻያ የሚደረግበትን ጉዳይ እና ምክንያቱን ፣

(ሐ) ማሻሻያ እንዲደረግበት የተጠየቀው ጉዳይ የሚያስከተለው የግንዘብ ወይም ሌላ ለውጥ፣

(መ) በሚሻሻለው የታክስ ስሌት የተገለፀው የታክስ መጠን ወይም ወደፊት የሚሸጋገር ኪሣራ ወይም በብልጫ የተከፈለ የግብዓት መጠን የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡

ሳበረ ሳበበ መን
የሚኒስትር ሐሳ

2/ የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ እንዲሻሻል የሚቀርበው ማመልከቻ ለማሻሻያው ምክንያት የሆኑ ጉዳዮችን ከሚደግፉ አስፈላጊ ሰነዶች ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡

7. ማመልከቻው የሚቀርብበት ጊዜ

1/ ታክስ ከፋዩ የራስ የታክስ ስሌት እንዲሻሻል ለታክስ ባለሥልጣኑ ማመልከቻ ማቅረብ የሚችለው የመጀመሪያው የራስ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት አምስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ነው፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ታክስ ከፋዩ የደረጃ "ለ" ግብር ከፋይ ከሆነ ወይም በፈቃደኝነት የሂሳብ መዝገብ የሚይዝ የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋይ ከሆነ የራስ የታክስ ስሌት እንዲሻሻል ለታክስ ባለሥልጣኑ ማመልከቻ ማቅረብ የሚችለው የመጀመሪያው የራስ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሶስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ነው፡፡

8. የውሳኔ አሰጣጥ

የታክስ ባለሥልጣኑ፡-

1/ የቀረበለትን የራስ ታክስ ስሌት ማሻሻያ ጥያቄ ማመልከቻ ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ ባሉት አንድ መቶ ሃያ ቀናት ውስጥ ጉዳዩ በሚመለከተው የሥራ ክፍል መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

2/ በቀረበለት ማመልከቻ መሰረት የራስ ታክስ ስሌት ማሻሻያ እንዲደረግ የፈቀደ እንደሆነ የታክስ ስሌቱን በማሻሻል ለታክስ ከፋዩ የተሸሻለውን የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ይሰጣል፡፡

3/ የቀረበውን የራስ ታክስ ስሌት ማሻሻያ ጥያቄ ያልተቀበለው እንደሆነ ያልተቀበለበትን ምክንያት በመግለጽ በጽሁፍ ለታክስ ከፋዩ ያሳውቀዋል፡፡

4/ የራስ ታክስ ስሌት ማስታውቂያ አዲት እየተደረገ ባለበት ጊዜ፣ ታክስ ከፋዩ የራስ ታክስ ስሌት ማሻሻያ ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ፣ የቀረበው ማመልከቻ አዲት

ሳበረ ኃበበ መ..
የሚኒስትር ሪ.

እያደረገ ላለው የሥራ ክፍል ተመርቶ ተገቢው ውሳኔ ከአዲት ውጤቱ ጋር ይሰጠዋል፡፡

9. <u>የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያን በድጋሚ ስለማሻሻል</u>

የታክስ ባለሥልጣኑ ታክስ ከፋዩ ባቀረበው ጥያቄ መሰረት የራስ ታክስ ስሌት እንዲሻሻል ወስኖ የተሻሻለውን የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ከሰጠ በኋላ በአዋጁ አንቀጽ 28 መሠረት ለታክስ ከፋዩ እንደገና የተሻሻለ የታክስ ሰሌት ማስታወቂያ ከመስጠት አያግደውም፡፡

10. <u>የራስ ታክስ ስሌት ማሻሻያ ጥያቄ የሚከለከልባቸው ሁኔታዎች</u>

1/ የታክስ ባለሥልጣኑ አጠቃላይ አዲት ወይም ኢንቨስቲጌሽን አዲት በማድረግ የተሻሻለ የታክስ ስሌት ማስታውቂያ ካወጣ በኋላ ታክስ ከፋዩ የሚያቀርበው የራስ ታክስ ስሌት ማሻሻያ ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

2/ አንድ ጊዜ የታክስ ስሌት ማሻሻያ እንዲደረግ ጥያቄ የቀረበበት የራስ ታክስ ስሌት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 መሠረት ውሳኔ ከተሰጠበት በኋላ በድጋሚ ማሻሻያ እንዲደረግበት ጥያቄ ሊቀርብበት አይችልም፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተመለከተው ቢኖርም የታክስ ባለሥልጣኑ በራሱ አነሳሽነት የተሻሻለ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ሊሰጠው ይችላል፡፡

<u>ክፍል ሶስት</u>

<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

11. <u>የተሻረ መመሪያና ተፈጻሚነት የሌላቸው አሰራሮች</u>

1/ ታክስ ከፋዩ ያቀረበውን የራስ ታክስ ስሌት ማስታውቂያ እንዲሻሻል ስለሚፈቀድበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 144/2011 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

2/ ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም አሠራር መመሪያው በሚሸፍነው ጉዳይ ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

ሳቢረ ሳባባ መ..
የሚኒስትር ሕ"

12. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በሚኒስትሩ ጸድቆ በሚኒስቴሩ ድህረ ገፅ ከተጫነበት ጊዜ ጀምሮ የጸና ይሆናል ::

አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ

ጥር 2015 ዓ.ም



ዓይናለም ንጉሴ አለ.
ሚኒስትር

ዓይናለም ንጉሴ ዓሊ

የገቢዎች ሚኒስቴር

ሚኒስትር